

‹‹ምን ሁናችኋል?!
መገጭ እንዴት ብሎ በክረምት
ሊጠራ ይችላል?!››



# አልማ እና የአውራ አምባ ማህበረሰብ

ዛሬ ዛሬ የእህል ወፍጮ መካከለኛ ገቢ ያላቸው የከተማና የገጠር ነዋሪዎች ሁሉ በቀላሉ እየገዙ ለየአካባቢያቸው አገልግሎት የሚያውሉት የንግድ ዘርፍ ነው፡፡ ቀደም ሲል ግን በጥቂት ከተሞች ካልሆነ በቀር በተለይም በገጠሩ ክፍል ያልተስፋፋ ነበር፡፡

ይህንን ችግር በመረዳት አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) በአማራ ብሔራዊ ክልል የተለያዩ የገጠር ክፍሎች ከ38 በላይ የእህል ወፍጮዎችን መትከሉን እናስታውሳለን፡፡ እነዚህ ወፍጮዎች የገጠር ነዋሪዎችን ሥራ ፈትተው ራቅ ወዳሉ ከተሞች ወፍጮ ፍለጋ ከመሄድ የታደጓቸው፣ ሴቶችን ከድንጋይ ወፍጮ ከሚያታግልና መጅ ከሚያስገፋ የሥራ ጫና የገላገሏቸው መሆናቸውን ለመረዳት አያዳግትም፡፡ ይህን መሰል ማህበራዊ ችግር ከማቃለል በተጨማሪም፣ በአልማ ወፍጮ ለተለገሳቸው ማህበረሰቦች ሁሉ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታም ነበራቸው፡፡ የአውራ አምባ ማህበረሰብ አባላት ግን



እሷም ሆነች እሱ ጠምደው ያርሳሉ።
እሱም ሆነ እሷ ቀጭን ይፈትላሉ።

ከአልማ የተሰጣቸውን የእህል ወፍጮ ጠቀሜታ የሚለኩት ከዚህ እጅግ በላቀ ሚዛን ነው።

ለዚህ መፅሔት ዝግጅት መረጃ እናጠናቅር ዘንድ ወደ አውራ አምባ ቀበሌ ጎራ ብለን ነበር። በልዩ የአኗኗር ዘይቤአቸው የሚታወቁት የአውራ አምባ ማህበረሰብ አባላት የሚኖሩባት ልዩ ጎጥም ‹‹ጡረኝ›› ወይም ‹‹ታይካ›› መሰኘቷን በእንግድነት ከተቀበለችን ወይዘሮ ከተረዳን በኋላ የተሳካ ጉብኝት ልናደርግ ችለናል።

ወይዘሮ እናነይ ክብረት የማህበረሰቡ እንግዳተቀባይናአስጎብኝመሆኗንም ነግራናለች። ከወይዘሮ እናነይ ጋር ቃለ ልውውጥ እያደረግን እያለን ‹‹ከአልማ የተሰጠቻችሁ ወፍጮ ዛሬም ድረስ ትኖር ይሆን? ›› የሚል ጥያቄ አነሳን። መልሷም ‹‹ባትኖርም ትኖራለች›› የሚል ነበር። ውሉን ያልለየ፣ ‹‹አለች›› ወይም ‹‹የለችም›› የሚል ቁርጠኛ ቃል ያልሰጠ፣ ባለ መንታ መንገድ መልስ መስሎ ታየን። ፈረንጆቹ Paradoxical የሚሉትን ዓይነትና እርስ በርሳቸው በሚቃረኑ ሃሳቦች የተዋቀረ፣ ነገር ግን የተጋጩ የሚመስሉትን ሃሳቦች የሚያስታርቅ ምክንያታዊ ትንታኔ የሚሻ መልስ እንደሚሆን በመገመታችን ችላ ብለን አልዘለልነውም። እንዲያውም የጉጉት ስሜት ጭሮብን ቀልባችንን ሰጥተን ልናስተባቃው ችለናል። እንዲብራራልንም ጠየቅን።

ወይዘሮ እናነይ ክብረት ማህበረሰባቸው ያለፈበትን የኋላ ታሪክ መነሻ ካላደረገች ይህን ጉዳይ አግባብ ባለው ሁኔታ ማስረዳት እንደሚያዳግት አሳሰበችንና የሆነውን ሁሉ ተረከችልን። ከሰባት ዓመት በፊት አልማ በተከለላቸው የእህል ወፍጮ የተነሳን ጥያቄና 21 ዓመት ወደ ኋላ ተንደርድሮ የሚጀምር መልስን ምን ግጥም ያገጣጥማቸዋል? ለማንኛውም ወይዘሮ እናነይ ክብረት ወደሰጡን መልስ እንሸጋገር።

‹‹የአውራ አምባ ማህበረሰብ አባላት አሁን ከምንገኝበት መንደር ተፈናቅለን በ1980 ዓ.ም ወደ ደቡብ የአገራችን ክፍል ወደ ቦንጋ ተሰደን ነበር። ለስደቱ መነሻው ‹የዚህን አካባቢ ሕብረተሰብ ባሕል አትቀበሉም› መባላችን ነው። በእርግጥ አውራ አምባዎችን ከሌላው የሚለዩን አስተሳሰቦችና ድርጊቶች አሉን። ዋናዎቹ አራት ናቸው።

‹‹በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሴቶችና ወንዶች እኩል እንደሆኑ



*ወ/ሮ እናነይ ክብረት*
*የአውራ አምባ ማህበረሰብ እንግዳ ተቀባይና አስጎብኝ*

እናምናለን። ፈጣሪ ሰውን አልከፈለም። ሴቶች ከወንዶች የሚለዩት በማርገዛቸው፣ በመውለዳቸውና በማጥባታቸው ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ልዩነት እንጂ እኩል አለመሆን አይደለም። ስለዚህም፣ የወንድና የሴት ተብሎ የተከፈለ ሥራ የለንም። ሁላችንም የቤት ውስጡንም ሆነ የውጪውን ሥራ እንሰራለን።

‹‹ይህን ሲቃወሙን ‹ሴት እኩል ከሆነች ማን አዛዥ፣ ማን ታዛዥ ሊሆን ነው? ወንድ ወደ ማጀት ገብቶ ሊያበስል ነው ወይ? ከሚስቱ ተጣልቶ ሽሽታ ወደ ማጀት ብትገባ እንኳን አይከተላትም። ቢርበው ከማጀት ገብቶ ሞሰብ ከፍቶ አይበላም› ይሉናል።

‹‹ሁለተኛው፣ የሕፃናት መብት መከበር እንዳለበት እናምናለን። በዚህም፣ ‹ልጅ የሰጡትን ይብላ፣ ያዘዙትን ይሥራ እንጂ የምን የልጅ እኩልነት ነው› በሚል ይቃወሙናል።

‹‹አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞችን የመደገፍ ኃላፊነት እንዳለብን ስለምናምንም በተግባር እንፈፅመዋለን። ሌሎች ግን ‹ማን የማንን አረጋውያንና አካል ጉዳተኛ ይጦራል? ከተወሰነ የዘር ትውልድ በኋላ ዘመድ አይደለም፣ ምናችንም አይደለም› ይላሉ። በአውራ አምባ እምነት ግን ዘር በዛ እንጂ ግንዱ አልተለወጠም።

‹‹አለመስረቅ፣ አለመዋሸት፣ አለመጉዳት፣ በራሳችን እንዲሆን የማንፈልገውን በሌሎች ላይ አለመፈፀም የመሳሰሉት የምንከተላቸው የሥነ-ምግባር መመሪያዎቻችን ናቸው። ይህን የሚቃወሙንም ‹ውሸት የገበያ መሸጫችን ነው። እየራበኝ እናንተ ልትበሉ ነው ወይ? ከራበኝ እሰርቃለሁ። ሃሜት ይጥፋ የምትሉት ቡና ስንጠጣ ምን እናውራ? ምቀኝነት እንዴት ከሰው ላይ ሊጠፉ ይችላል?› እያሉ ነው።

‹‹ከዚህ በተነሳ ‹ባሕላችንን አቆሸሹ፣ አጠፉ ተብለን ጉዳዩንም ወደ ፖለቲካ አዙረው፣ የመንግሥት ተቃዋሚ ናቸው አሉን። የደርግ መንግሥትም በእኛ ላይ ግድያ መፈፀም ጀመረ። በተለይም በማህበረሰቡ መሥራች ዙምራ ላይ ልዩ ትኩረት አድርገው ነበር። በዚህ ምክንያት ነው ከዚህ ጠፍተን የሄድነውና ወደ ደቡብ የተሰደድነው።

‹‹ኢሕአዴግ ከገባ በኋላ ግማሾቻችን በ1985 የተቀሩት በ1986 ዓ.ም ተመልሰን መጣን። የመጀመሪያ ቦታችን ላይ ስንሰፍር ሰው መሬታችንንና ንብረታችንን ተከፋፍሎ ጠበቀን። ተመልሰንም ‹እስኪ የአሁኑ መንግሥት ያድናችሁ እንደሆነ እናያለን› እያሉ እኛን የማጥቃት ሙከራም ያደርጉ ነበር። በገበያም ምንም ነገር አይሸጡልንም። ወደ ወፍጮ ሄደንም እህል ማስፈጨት አንችልም።

‹‹አልማ በ1994 ዓ.ም የእህል ወፍጮ ተከለልን። ከወፍጮ ቤትም እንዳንደርስ ተከልክለን በተገለልንበት ጊዜ ከአልማ ወፍጮ ማግኘታችን እጅግ የተለየ ስሜት የሚፈጥር ድጋፍ ነው።

‹‹ይህ ብቻ አይደለም። ወፍጪችን ስትጮኽ የአካባቢው ሕብረተሰብ መስማት ጀመረ። በቅርባቸው የሚገኝ ወፍጮ ስለሆነ ወደ እኛ እየመጡ ማስፈጨትን ምርጫቸው አደረጉ። እህላቸውን ሰጥተውንም ወደ የሥራቸው ይሄዳሉ። ፈጭተን እንጠብቃቸዋለን። በፍቅር ስለምናስተናግዳቸውና በአደራ የሰጡንን የሚፈጭ እህልና ሥራ ሳናጓድል በሙሉ ታማኝነት ስለምናስረክባቸው ለማስፈጨት ብለው ሥራቸውን አያስተጓጉሉም።

‹‹በዚህ ዓይነት ሂደት እየተግባባንና እየተቀራረብን ሄድን። ለማስፈጨት መምጣታቸው ማንነታችንን እንዲያውቁ ረዳቸው። በአሁኑ ጊዜ ሕብረተሰቡ ለእኛ ያለው ፍቅርና አክብሮት በጣም ከፍ ያለ ነው። ሴቶቹም እንደእኛ ማህበረሰብ ሴቶች ጠምደው ማረስ ጀምረዋል። ወደኛ እየመጡም ሸቀጣሸቀጥ ይገዛሉ። የበፊቱ ድርጊታቸው እየቆጫቸው ‹እኛ እድሜያችንን በከንቱ ፈጀነው፣ ለልጆቻችን መሰረቶቻቸው ናችሁ፣ እናንተን ያቀይልን› ይሉናል።



ከአልማ የተበረከተች የመጀመሪያዋ የአውራ አምባ ማህበረሰብ የእህል ወፍጮ ሞተር

‹‹ስለዚህ፣ አልማ የተከለልን ወፍጮ በተገለልን ጊዜ ለችግራችን ደራሽ ሆናለች፡፡ በአሁኑ ጊዜም የአልማ ወፍጮ ዘር ተክታ 5 ሌሎች ወፍጮዎች አሉን፡፡ የአልማ ወፍጮ ‹‹ተበራክታለች›› እንጂ ‹‹የለችም›› አትባልም፡፡ ራሷም አለች፡፡ የማንጠቀምባት በናፍጣ የምትሰራ ስለሆነችና መብራት ስለገባልን ነው፡፡ እሷ የተካቻቸው ግን በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ናቸው፡፡ የመጀመሪያዋን የአልማ ወፍጮ የመብራት ጄነሬተር ልናደርጋት እያሰብን ነው፡፡ መብራት ሲጠፋ ለጤና ኬላና ለመሳሰሉት ልታገለግል ትችላለች፡፡

‹‹የአልማ ወፍጮን ከገንዘብነቷና ብዙ ገንዘብ ያፈራች ከመሆኗ በላይ ትልቅ ትርጉም የሚያስጣት ግን ከአካባቢው ሕብረተሰብ እንድንገናኝ፣ እንድንግባባ፣ እንድንዋደድ ያደረገች መሆኗ ነው፡፡ እሷ ለዘለዓለም የሚኖር የሰላምና የፍቅር መሠረት ስለጣለች፣ ነገ በማትኖርበት ጊዜም ትኖራለች፡፡ ዘላላማዊ ናት፡፡››

ወይዘሮ እናነይ ክብረት አልማ የጤና ኬላ እንደገነባላቸው፣ አንድ የማህበረሰባቸው ወጣት የመሰናዶ ትምህርቱን እንዲከታተል ሙሉ ድጋፍ አድርጎለት ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት መብቃቱንና በ2001 ዓ.ም መመረቁንም በዚህ አጋጣሚ ሳትገልፅ አላላፈችም፡፡ ይህን መነሻ በማድረግም፣ አልማ በማህበረሰባቸው ውስጥ ባከናወናቸው ጤና ነክ ተግባሮች ላይ ያላቸውን አስተያየት ይሰጡን ዘንድ ከሌሎች ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡





የአልማ ወፍጮ ካበረከተቻቸው 5 የአውራ አምባ ማህበረሰብ ወፍጮዎች አንዷ

# ‹‹ያዋለደችኝ የወለደችኝ እናቴ ነች፡፡››



ወ/ሮ መርከብ ዑመር

አዋላጅን ጠይቀን ወላድን ሳንጠይቅ መቅረት ጎዶሎ የሚያደርገን መስለንና፣ በቅርብ ቀን የወለደች ሴት በሰፈሩ ካለች ያገናኙን ዘንድ ጠይቀንም ነበር፡፡ ለጥያቄያችን አዎንታዊ መልስ ያስገኘልን መልካም አጋጣሚ አላጣንም፡፡ ከወለደች 15 ቀን የሆናት ሴት ነበረችና ቤቷ ድረስ ሄደን አራስ ጠያቂ ለመሆን በቅተናል፡፡ ‹‹እንኳን በሽልም ወጣሽ!›› አልናትም፡፡ ወይዘሮ መርከብ ዑመር ሴት ልጅ መገላገሏንና 3ኛ ልጇ መሆኗን አብስራልን፣ በማስከተልም ‹‹በእርግዝናሽ ዘመን የገጠመሽ ችግር ነበር ወይ?›› ስንል ጠየቅናት፡፡ እንዲህ ስትልም መለሰችልን:-

‹‹በዘንድሮው ዓመት በእርግዝናዬ ላይ የተለየ ችግር ነበረብኝ፡፡ የሽሉ አቀማመጥ ትክክል አልነበረም፡፡ ምግብ አላስወስድ እያለ ነበር የሚያስቸግረኝ፡፡ አልማ የጤና ኬላ ስለሰራልንና ሃኪም ስላለን ግን የሚከታተለኝ አላጣሁም፡፡ ሃኪሞች መመገብ ያለብኝን እየነገሩኝ የምክር አገልግሎት ሰጥተውኛል፡፡ ምክራቸውን ተግባራዊ አድርጌአለሁ፡፡ ጠቃሚ ሆኖም አግኝቼዋለሁ፡፡

‹‹ደም ያንሰኝ ነበር፡፡ በአመጋገብ አስተካከልኩት፡፡ ለሽሉ መጠንከር የሚበጅ አመጋገብንም በሃኪሞቹ ምክር ተግባራዊ አድርጌዋለሁ፡፡ በሽሉ አቀማመጥ ላይ ያለውን ችግርም ነርሷ በእጇ እየነካካች በማደራጀት ታስተካክልልኝ ነበር፡፡”


ከወይዘሮ መርከብ ዑመር እንደተረዳነው፣ በእርግዝናዋ ዘመን ለነበረባት ችግር መፍትሄ የሚሆን የሃኪሞች ክትትል ስላልተለያት በወሊድ ጊዜዋ ችግር እንዳይገጥማት ረድቷታል፡፡

‹‹ስወልድ የጠና ችግር አላጋጠመኝም፡፡ በአጋጣሚ እናቴ ኑርሃያት አህመድ የልምድ አዋላጅ የነበረችና በኋላም በአልማ የሰለጠነች ናት፡፡ ያዋለደችኝ የወለደችኝ እናቴ ነች፡፡

‹‹ዋናው በቀላሉ እንድወልድ ያደረገኝ በእርግዝናዬ ጊዜ የሃኪም ክትትል ስላልተለየኝ ነው፡፡ አልማ ያቋቋመልን የጤና ኬላ ጥሩ አገልግሎት እየሰጠን ይገኛል፡፡ ሁሉም እናቶች በእርግዝና ጊዜ የክትትል አገልግሎት ያገኙበታል፡፡ የምክር አገልግሎት ይሰጥበታል፡፡ በወሊድ ጊዜያቶች በሰላም እንዲገላገሉ የሚያደርግ የጤና ኬላ ነው፡፡ ከእኛ ሃኪሞች አቅም በላይ ከሆነም ሪፈር ፅፈው ከፍ ወዳለ የህክምና ጣቢያ ይልካሉ፡፡

‹‹አልማ የሰራልን የጤና ኬላ እናቶች ጤነኛ ሆነን ለሥራ እንድንሰማራ፣ ጤነኛ ልጅ እንድንወልድ እያደረገልን ነው፡፡››

# ‹‹ልጅ በጤነኛነት ይወለዳል፡፡ ልጅ ከተወለደ በኋላ ባለው ጉዳይ ላይ ግን ራሳቸው ከእኛም የበለጡ ናቸው፡፡››





ሲስተር ሙላውላንቺ አምሳሉ



አውራ አምባዎች ቀደም ሲልም በራሳቸው ተነሳሽነት የሠሩት የጤና ኬላ ነበራቸው፡፡ አልማ የተሻሻለ አዲስ የጤና ኬላ ሲሰራላቸው ግን የሚያገኙት የጤና አግልግሎትም የተሻለ ሊሆን ችሏል፡፡ ይህም ሆኖ፣ የጤና ኬላቸው የአግልግሎት ደረጃ ከፍ እንዲልላቸው አበክረው ይጠይቃሉ፡፡ በእነዚህና መሰል ጉዳዮች ላይ ያነጋገርናት ደግሞ ሲስተር ሙላውላንቺ አምሳሉ ነበረች፡፡



አውራ አምባዎች የሠሩት የቀድሞው የጤና ኬላ



በአውራ አምባ ማህበረሰብ መንደር ለማህበረሰቡና ለአካባቢው ነዋሪዎች በአልማ የተሰራ አዲስ የጤና ኬላ

ሲስተር ሙላወላንቺ ከየካቲት ወር 2000 ዓ.ም ጀምሮ አልማ በሰራው የጤና ኬላ ውስጥ ለአውራ አምባ ማህበረሰብ አባላትና ለአካባቢው ነዋሪዎች የህክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ የምትገኝ ነርስ ነች። ሲስተር ሙላወላንቺ ስለእናቶችና ህፃናት ጤንነት ስትናገር:-

‹‹በአውራ አምባ ማህበረሰብ ውስጥ በአወላለድ ላይ ጥሩ ለውጥ አለ። ልጅ በጤነኛነት ይወለዳል። ልጅ ከተወለደ በኋላ ባለው ጉዳይ ግን ራሳቸው ከእኛም የበለጡ ናቸው። ለሕፃናት መብትና አስተዳደግ እጅግ ጠንቃቃ ናቸው›› ትላለች።

ለጤና ኬላው መሟላት ያለበት ተጨማሪ ነገር እንዳለም ሳትጠቁም አላለፈችም፤ እንዲህ በማለት:-

‹‹አካባቢው ታይፎይድና ወባ ይበዛበታል። ሁለቱንም በግምት ለመለየት እየሞከርን ህሙማኑን ወደ ወረታ እንልካቸዋለን። የሁለቱ በሽታዎች ምልክት (Symptom) ስለሚመሳሰል በእርግጠኝነት ታይፎይድ ወይም ወባ መሆኑን ለመለየት እንቸገራለን። ይህ ችግር የሚያጋጥመን ላቦራቶሪ ስለሌለን ነው።

‹‹ይህን ጤና ኬላ የ31 ጎጦች ነዋሪዎች ይገለገሉበታል። የራሱ ላቦራቶሪ እንዲኖረው እንፈልጋለን። ሌላ ችግራችንም የመድሃኒት አቅርቦት አለመሟላት ነው። ላቦራቶሪውን በተመለከተ ከአማራ አቀፍ ልማት ማህበር ቃል እንደተገባ ሰምቻለሁ።››

# ‹‹...በመንገድ አርገህ ና››

## አልማ በመንገድ ግንባታ ዘርፍ ያከናወናቸው ተግባራት

1. በሰሜን ጎንደር ዞን ከደባርቅ ሳንቃ በር /ሰሜን ፓርክ/ 16 ኪ.ሜ. ጥገና
2. ምዕራብ ጎጃም ዞን ጢስ ዓባይ ከተማ ጢስ ዓባይ ድልድይ 1.6 ኪ.ሜ.
3. ምሥራቅ ጎጃም ዞን ከሮብ ገበያ ድጎ ጽዮን አስቸጋሪውን የጨቄ ተራራ አቋርጦ የሚያልፈው የ53 ኪ.ሜ መንገድ
4. ሰሜን ጎንደር ከሳንጃ ማሰሮ በአስቸጋሪው የሳንጃ ወንዝ ላይ ከ38 ሜትር በላይ ርዝመት ያለው ድልድይ የተገነባለትና የተንፈልን ተራራ አቋርጦ የሚያልፈው 42 ኪ.ሜ መንገድ
5. በዋግ ኽምራ ዞን የተሠራው ድልቢያ ቅዳሚት 18 ኪ.ሜ መንገድ
6. ሰሜን ወሎ ዞን በዳውንት ወረዳ የተሠራው 32 ሜትር የኮን የኔንጃ ድልድይ (የእንጮቄ ወንዝ ድልድይ)

*አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) ከተመሠረተ ጀምሮ በክልሉ ውስጥ የሰራቸው የገጠር መንገዶች ስድስት ይሆናሉ፡፡ አልማ የሠራቸው መንገዶች ቁም ነገር የሚመዘነው ግን በፕሮጀክቶቹ ብዛት ወይም በኪሎ ሜትር ርዝመታቸው አይደለም፡፡*

*አልማ እጅግ አስቸጋሪ ወደሆኑ የገጠር ክፍሎች እየገባ የሚሰራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ውስብስብ የዘመናት ችግር ወደቀየዳቸው የገጠር አካባቢዎች እየገባ የሚያከናውናቸው የልማት ተግባሮች ደግሞ ‹‹የአልማ ምልክቱ ፅናቱ!›› እንድንል ያስገድዱናል፡፡ የሠራቸውን መንገዶች ትርጉም ትልቅ የሚያደርገውም ከፍ ያለ ቁርጠኝነትና ፅናትን የሚጠይቁ ከመሆናቸው በላይ፣ በአገር ውስጥ እያሉ ከአገር ተነጥለው ለኖሩ አካባቢዎች የመገናኛ በር የከፈተ፣ ከመከራና ከሰቆቃ ኑሮ እያላቀቀ ለተሻለ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጥ ያበቃ መሆኑ ነው፡፡*

*ይህን በጥልቀት መረዳት ይቻል ዘንድም ከተሠሩት መንገዶች መካከል ከፊሎቹን በማንሳት ፋይዳቸውን መመልከት ተገቢ ሳይሆን አይቀርም፡፡*

## 1. ከሳንጃ ማሰሮ ደንብ

ከሳንጃ ተነስቶ ማሰሮ ደንብ የሚያደርሰውና በፈረንሳይ ኢምባሲ ትብብር በአልማ የተሠራው 42 ኪሎ ሜትር የክረምት ከበጋ መንገድ ከፍተኛ ወጪ ወጥቶበታል፡፡ የመንገዱ ሥራ የተጠናቀቀውም በርካታ በማህበረሰቡ ውስጥ የኖሩ ኋላ ቀርና የጥርጣሬ አስተሳሰቦች በፈተናነት ታልፈው ነው፡፡

እንደሚታወቀው፣ ታች አርማጭሆ የኃይለ ሥላሴም ሆነ የደርግ መንግሥታት አስተዳድረውት አያውቁም፡፡ አንድም ዓይነት የመንግሥት መዋቅር ሳይኖርበት፣ የራሱን የጎበዝ አለቃ እየመረጠና እየሾመ በራሱ ፈቃድ የኖረ ሕዝብ ነው፡፡ ያለፉት መንግሥታት ‹‹ታች አርማጭሆ ሽፍታ ነው፣ አመጸኛ ነው›› እያሉት በዓይነ ቁራኛ እየተመለከቱት በመኖራቸው፣ የወረዳው ሕዝብ የንግድ ግንኙነት በዋነኛነት በስተምዕራብ ከሚያዋስነው ከሱዳን ጋር ነበረ ለማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህም፣ ታች አርማጭሆ የራሷ ዳር ድንበርና ሉአላዊነት ያላት አገርን ተመስላ በመሰላት መንገድ ስትተዳደር ለዘመናት የኖረች ወረዳ ነች፡፡

ታች አርማጭሆ የአገራችን አንድ ወረዳ ሆና ተዋቅራ፣ ሕዝቧም የመንግሥት አካል ሆኖ መተዳደር የጀመረው ከ1983 ዓ.ም በኋላ ነው፡፡ ይህን ‹‹ታች አርማጭሆ እናት አገሯን ተቀላቀለች›› ሊባልለት የሚችልን አዲስ ምዕራፍ ተከትሎም፣ የሳንጃ ማሰሮ ደንብ መንገድ በአልማ ተገነባና ተዘግቶ የኖረው በር ተከፈተ፣ ጀርመንን ከሁለት ከፍሎ በኖረው ግንብ የመሚመስለው አጥር ፈረሰ፡፡

ይህም ሆኖ ያለፉት መንግስታት ከፈጠሩባቸው የጥርጣሬ መንፈስ ጋር የሚኖሩና በዚህም ምክንያት የመንገዱን መሠራት የሚቃወሙ አልታጡም ነበር፡፡ አልማ መንገዱን ለመስራት ሲያቅድ በቅድሚያ ሕዝቡን ያወያየ ሲሆን፤ ስብሰባውን የመሩትም የማህበሩ የወቅቱ ሊቀመንበርና ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሕላዌ ዮሴፍ ነበሩ፡፡

በዚህ ጊዜ “መኪና መንገድ ሠርታችሁ ስናኮርፍ መደበቂያችንን ልታስደፍሩት ነው ወይ?” ያሉና የአቶ ሕላዌን በትጥቅ ትግሉ ሠቅት በአካባቢው እንደነበሩ በማስታወስም “እናንተም ትግላችሁን ያካሄዳችሁት እዚህ ነው፡፡ እናም መንገድ ተሰራ ማለት ማጀታችን ተደፈረ ማለት ነው” ሲሉ የተቃውሞ ድምፅ ያሰሙ መኖራቸውን እናስታውሳለን፡፡ ሌሎች ደግሞ “እስከመቼ ድረስ በጨለማ ውስጥ እንኖራለን፤ ስልጣኔ ያስፈልገናል፤ መንገዱ መሠራት አለበት” ሲሉ ጠንክር ያለ አስተያየት ሰነዘሩ፡፡ በመጨረሻም መንገዱ እንዲሰራ ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡